ክፍል አንድ

ፍለጋ

ገቢር 1 (አንዱ)

መጋረጃ ሲከፈት ዳንኤል ፣ ግርማ ፣ ታምሩ ሻንጣ እያስተካከሉ ይታያሉ

/ከውስጥ ትወጣለች ማርታ /

ማርታ ፡ የሚተርክልኝ የደግ ዘመን ታሪክ ልክ በስራ ላይ እንዳታውይ የተባልኩ ይመስል እንደገደል ማሚቶ እየደጋገምኩ መኖሬ ሲሰለቸኝ . . . ፈልጌ እንኳን አገኘሁ እንደሆነ አልጓጓም . .

/አይኗን ወደፊት ትወረውርና ደጉን ዘመንና ሰዎቹን በአይነ ህሊናዋ ውስጥ ትስላቸውና /ሹመትን ፣ ሽልማትን ፣ሙገሳንና ውዳሴን ሰይሆን . . . ስለ በደለ ፋንታ የተደረገላቸውን እውነተኛ ፍቅር በማሰብ . . . የስም ሳይሆን የግብር ክርስቲያኖች ለመሆን የእግዚአብሔን ክብር የሻታችሁ /ዘመነ ሐዋርያት እያለች ትጠራዋለች /ስለ ፍቅር ነገርን የሰወራችሁ ስለ ፍቅር የበደልን ብድራት በምህረት የከፈላችሁ . .. . . ስለ ፍቅር ኃጢአትን የከደናችሁ እናንተ በአንድ መዕድ የተመገባችሁ . . . በረከት የተትረፈለፈላችሁ መረዳዳትን ፣መተዛዘንን ፣መፈቃቀርን ልብሳችሁ ያደረጋችሁ ደሳ ወገኞቹ (ወደ ፊት እየረራመዳችሁ እጇን ስትዘረጋ ዳንኤል)

ዳንኤል ፡ ማርታ ፡ ! ም . . . ምን

ማርታ ፡ (ፊቷን ወደነ ዳንኤል ትመልስና) እነሱ ይናፍቁኛል

ዳንኤል ፡ (በቁጭት) እነሱማ አለፉ . . . . ታሪካቸውን ትተውልን

ማርታ ፡ (አቀርቅራ ታስባለች እንዳቀረቀረች ታሪካቸውን ትተውልን (ቀና ትልና ወደ ህዝቡ በቁጭት) . . . አዎ ታሪክ በታሪክነቱ የሚተርከው እንዲደገም እንጂ ተተርኮ ብቻ እንዲቀር አልነበረም ላዘውም ‹‹በእኔ ያመነ እኔ የምሰራውን ሁሉ ይሰራል ይበልጥም ያደጋል ያለውን የአምላክ ቃል በተግባር የፈፀመ የግብር ሰዎች ታሪክ . .. . ወይኔ ! (ግንባሯ መትታ) ወይኔ ! (ዞር ብላ ወደ ነዳንኤል)ግርማ ታሪክን መድገም ሲያቅተኝ ዘመኑን ለማየት አልናፍቅም ?

ግርማ ፡ ምን አንቺ ብቻ (ወደ ህዝቡ ዞር) ሁላችንም (ሻንጣውን እያስተካከለ) ጨረስን መሰለን (ወደ ማርታ እየተመለከተ)

ማርታ ፡ ዳንኤል (በአይኗ የእንሂድ አይነት ምልክት እያሳየች)

ዳንኤል ፡እሺ (ሻንጣውን አንስቶ ወደ ፊት እየተመለከተ) ፍለጋ !

ማርታ ፡ ዘመነ ሐዋርያት (ወደ ህዝቡ እያየች)

ግርማ፡ ፍለጋ

ገቢር 2 (ሁለት)

(መጋጃ ሲከፈት በእድሜ የገፋ የቤተ ክርስቲያን አባት ከወጣቶች መሀል ቁጭ ብለው ሲነጋገሩ ይታያል መንፈሳዊ ክላሲካል ይሰማ ክላሲካ ሲቆም)

አባ ፡ (ሁሉንም በአይናቸው እየቋኛቸው) እናንተ ሁላችሁም ደጉን ዘመን ናፋቂዎች ናችሁ

ታምሩ ፡ አዎ አባ . . . . . ደጉን ዘመን እና ደጎቹን ሰዎች ናፋቂዎች ነን (አይኑን ወደ መንገዱ እየወረወረ) ሌሎቹም መጡ አባ ! . . . ደጉን ዘመን ፈላጊዎቹ መጡ ወደ አባ እያየ (እነ ማርታ እያወሩ ነው የሚመጡት ልክ ከእነ አባ ያሉበት ሲደርሱ ማርታ ድምጸ ከፍ አድርጋ

ማርታ፡ የተፀነስኩበትን ሌሊትና የተወለድኩበትን እለት ልርገመው (ወደነዳንኤል ዞራ)

አባ ፡ ለምን (በማዘን አትኩረው እያዩኡት)

ማርታ ፡ ታሪክ ደጋሚ ሳይሆን ተሪኪ ብቻ ሆኜ ስለቀረሁ . . . . (ሰላምታ ትሰጣላችሁ) አባ (እየጠረጠራቸው ትቀመጥና) ደጉ ዘመንና ደጎቹ ሰዎች በሌሉበት ዘመን ለምን ፈጠረን

አባ፡ አይ ልጄ እግዚአብሔር አምላክ ደግ ዘመንና ክፉ ዘመን ደግ ሰውና፣ ክፉ ሰው እያለ አልፈጠረም ነበረ . . . ዘመኑን ደግና ክፉ የምናደርገው) እኛው በአምሳሉ የተፈጠርን የሰው ልጆች ነን ግን ግብራችን የከፋው (ግንባራችውን ክስክስ አድርገው)

ማርታ ፡ /በቁጭት /አንዴ ወደፊት አንዴ ወደ ሰማይ እያየች / ታዲያ ግብራችን ከፍቶ ዘመኑን ስናስወቅስ ለምን ፀጥ ይለናል ? . . . . .. .ሰው ሆነን ተፈጠረን የሰውነት ግብር ካልታየብን ለምን ዝም ብለን ያየናል ? . . . . .ድራሻችንን ከምድረ ገጽ አጥፍቶ ደጋጎችን ሰዎች ለምን አያኖርበትም !

አባ ፡ አይ ልጄ . . . .. ያላስታዋልሽው ነገር አለ . . .. . አየሽ አምላካችን እኮ ቃሉ የማይሻር . . . . . እውነተኛ አምላክና ዘላለማዊ አምላክ ነው እ. . . . . ክብሩን ዝቅ አድርጎ ወደዚህ ምድር መምጣቱ ፍቅር ስቦት እንደ ነበር ዘነጋሽው ? . . . . ታድያ ልጄ ዛሬ ግብራችን የከፋ ዘመን አስወቃሾች ከነ ጉድፋችን ሊያጠፋን ስላልወደደ ነው ያስቀመጠን . . . . ምን አልባት የንስሃ ሰዎች ይሆኑና ትህትናን በግብር እያሳዩ የደጎችን ሰዎች ታሪክ ደጋሚዎች ይሆናሉ ብሎ ስላሰበ ነው ዝም ያለን የመሰለሽ ::

ታምሩ ፡ አንገቱን ወደ ሰማይ ቀና እያደረገ) አዎ ! የማንንም ኃጢያተኛ ሞት እንዳማይወድ በነብዩ ሕዝቃኤል ላይ አድርጎ የተናገረው አምላካችን ዛሬም ይታገሰናል (ወደ ፊት እየተራመደ) እናንተ የደጉ ዘመን ሰዎች ስለ እናንተ ብሎ ዛሬ ተመለሱ ይለናል . .. . .(ወደ ፊት እየተራመድ እያየ) በኃጢአት ለተጎሳቆሉ ወገኖችን ምህረትን የለመንክ አባታችን አብርሐም ሆይ . . . .በወገኖች በደል እራስህን አሳልፈህ ሰጥተህ ወገኖችን ያስማርክ አባታችን መሴ ሆይ . . . . የአምላክን ቃል

ግብር ፈፅማችሁ አልጫውን አለም ያጣፈጣችኑ ሐዋርያት የነሱን ታሪክ የደገማችሁ አምላክን ያስደሰታችሁ ቅዱሳን አባቶቻችን (ሁሉም በህብረት በአንድ ድምፅ) ትናፍቁናላችሁ !

ዳንኤል ፡ አዎ መተሳሰብ ፣መረዳዳት ፣መተዛዘንና መፈቃቀር ወንጀል በሆነበት ዘመን እየኖርን ደጉ ዘመንና ደጉን ሰዎች ነው መናፈቃችን ሀጢአት አይሆንብንም (ወደ ፊት ይቆምና ወደ ፊት ይራመዳል . . .. ትኩር ብሎ በተመለከተ ቡኃላ ይጣራል / ዘመነ ሐዋያት . . . . . ዘመነ ሐዋርያት . . . . .አረ ዘመነ ሐዋርያት (ሁሉም ልጆች በየአቅጣጫው ተበታትነው ያያሉ

አባ ፡ / ብድግ ብለው ወደፊት እየተመለከቱ

ዘመነ ሀዋርያት

የክርስትና ጎህ የጧቱ

ተመልሰህ ና እንደገና

የጥዋው ማህበር ላልቷልና

ማርታ ፡ በአንድ ልብ መምከሩ በአንድ ቃል መናገሩ

ከቶ ጠፍቷልና ጨርሶ ከምድሩ

እባክህ ተመለስ ዛሬም እንደገና

መስረተ እምነት መቅድም ክርስትና

የሐዋርያት ዘመን የዘለአለም ፋና

ዘመነ (3) ሀዋርያት ትጣራለች

ዳንኤል ፡ በአንድ መሶብ ዙሪያ ተቀድሶ መብላቱ

ከአንድ ፅዋ ምንጭ ቀድቶ መጠጣቱ

የያኔው አሻራ የጥንት የጠዋቱ

ኧረ ለምን ይሆን በደብዝዞ መቅረቱ

የነደደው እሳት ፍቅር ፍም መቅረቱ

ፀሀይ፡ እንዳይተርፍ ተብሎ ስስት ተጀመረ

በረከት መባሉም ያኔ ድሮ ቀረ

መሶቡ ተነስቶ በእጅ ሆነ ገበታው

ተድበለበለና ቁርጥ ሆነ እንጀራው

ጸጋው መቁረጡን ማንም አላሰበው

ግርማ ፡ ለጴጥሮስ ሲያስረክብ ርስቱን እየሸጠ

የያኔው ክርስቲያን መች በራብ ተዋጠ

መቼ ጎድለበት መቼ ተንገላታ

በፍቅር ኖረ እንጂ አንዱም ሳይፈታ

በረከት በዝቶአለት በሙሉ ገበታ
ሐናንያ ሲፒራ ልባቸው የዋለለ
ወደ ገንዘብ ፍቅር ወዲያው ያጋደለ
በሊቀ ሐዋርያት በቅዱስ ጴጥሮስ ቃል
በመንፈስ ቅዱስ ጅራፍ ተቀጥተው ሞተዋል
በሰሙት ሁሉም ላይ ፍርሃት ሆኖ ቀርቷል ።።

ዳንኤል ፡ ዘመነ ሀዋርያት (3) ይጠራል ሁሉም በየአቅጣጫው ተበታትነው ያያሉ

ማርታ ፡ ቀዳሚት ተዋህዶ የሐዋርያት
የፍቅር ማህበር ጸጋ በረከት
አትራቂ አትሸሺ አትለይን በእውነት
ከፊት ምሪን እንጂ በመሆን አብነት
ሁሉ እዲወጣ በአንቺ ቸርነት
ጥዋና መሶቡን ዓለም ሲጥላው

ማርታ ፡ በእኛ ዘንድ ተገኘ የጥንት አሻራው
ሸክላ ስላለብህ እንዳይቀር አደራ
እንደገደማይቱ ኑ እንጂ በጋራ
ብርሃን ነውና የጧቱ ጮራ
ዘመነ ሐዋርያት (3) ትጣራለቸ

ታምሩ ፡ አባ መቼ ይሆን /ወደፊት እየተመለከተ / ይሄ የምንናፍቀው ደግ ዘመን የሚመለሰው . . . . . መቼስ ነው አቤት የሚለን

አባ ፡ አይ ልጄ . . . . ደጉ ዘመን መቼ ጠፋና ነው የሚመለሰው . . . . . መቼስ ራቀንና ነው አቤት የሚለን . . . . . የኛው በደልና ኃጢአት ሸፍኖት እንጂ እንግዲህ ልጆቼ /ሁሉን እያዩአቸው /ደጉን ዘመን ከናፈቃችሁ ራሳችሁን መርምሩ ከክፉት ፣ከበደል፣ ከኃጢአት . . . . ተጠበቁ . . ልጆች ክርስትና የዋዛ ጉዞ አይደለም ወደፊት /በተመስጦ እያዩ / እነዛ የምንናፍቃቸው ሰዎች በተጓዙበት መንገድ ለመጓዝ የግብር ሰዎች ሆነን መገኘት አለብን . . . . . ክርስትና ሲማሩት ብቻ ሳይሆን ሲኖሩት ነውና የሚተረጎመው . . . . . ክርስትና ራስን ትቶ ስለ ወገን ማሰብ ነውና . . . . ክርስትና ራስን ጎድቶ ወገንን መጥቀም ነውና ክርስትና ሌሎችን ሳይሆን ራስን ማየትና ክርስትና ራስን ከወንጀል ነፃ ለማድረግ ሳይሆን የወገኖችን በደል ተሸክሞ መወንጀልና ነውና . . . . .እንዲህ ካደረግን የምንናፍቀውን ዘመን ልናገኘው እንችላለን እኛም ታዲያ የደግ ዘመን ነዋሪዎችቹ ደጎቸ ሰዎች እንባላለን ።።

ግርማ ፡ /በመገረም / ዳንኤል . . . . . .ጥያቄው ተመለሰ ማለት ነው / እዚህ ላይ ከውስጥ ጥያቄው ከውስጥ ይደገማል / ዳንኤል ለማስታወስ ያቀረቅራል አስታውሰዋለሁ . . . . . .ይሔው ብዙም ሳንጓጓ እዚሁ ተገኘ

ዳንኤል ፡ አዎ ግርማ . . . . .መከሰስ ያለብን እኛው ነን . . . . . ደጉን ዘመንና ደጎቹን ሰዎች በክፉ ግብራችን አረም ውጠናቸው ጠፉ እያልን በማማታችን በስም አጥፊነት ወን ጀል ፍርድ ይገባናል ።

ታምሩ ፡- /አንገቱን በቀጭት / ልክ ብልሀል . . . . . ክፉን በደግ መመለስ ሲያቅተን ፣ የስነቱን ንጉስ ዙፋን በልባችን ዘርግተን መቸር ሲያቅተን ፣ . . . .ትጎትናን ገንዘባችን በማድርግ ሰው መሆን ሲያቅተን . . . . . ከክፉው ግብራችን መሸፈኛ ምክንያት ያድነን ይመስል ‹‹ ጊዜው ነው ! ዘመኑ ነው ! የሚለውን ቋንቋ እንደ ጥሩ አባባል እየተናገርን በእርሳችን እንሸነጋገላለን / /የብሽቀት ፈገግታ ፈገግ እንዴ ወደ ህዝቡ አንዴ ወደ እነሱ እየተመለከተ /ቆይ ጊዜውና ዘመኑ ምን አደረገ

ማርታ ፡-/ጣልቃ ትገባና / እንጃ ! . . . .መወቀስ ያለብን እኛው ነን / የብሽቀት ፈገግታ / ጊዜማ ሲፈጠር የተሰጠውን ትዕዛዝ እየመሸ እየነጋ ፣በጋና ክረምትንም እያፈራረቀ ዘመንን ያስቆጥራል . . . . እኛስ/ እንዴ ወደ ህዝቡ አንዴ ወደ ጌደኞቿ እየተመለከተች / እኛማ ባለንበት የማንረጋ ፣ ባየንበት የምናድር ወላዋይ ፣ በሰውነታችን ሳይሆን በንዋያችን ብዛት የምንከባር ፣ አጥቶ ነጠቶ የምናየው ወገናችንን የምናቋሸሽ፣ ነገ ምን ይመጣብናል ሳንል በዛሬው ብቻ የምንመካ ነንና ታሪክ መድገም አቃተን እናም ጉዞአችን የጎሊት ሲሆንብን ‹‹ ጊዜው ነው ደጉ ዘመን እማ አለፈ ›› እያልን ዘመን ናፋቂዎች ሆንን /እጇን አፏ ላይ አድርጋ በግርምት ወደ ፊት ስትመለከት

ግርማ ፡- ማርታ ናፍቀን አልቀረንም . . . . ፍለጋውን ከመጀመራችን በፊት ዳንኤል አንድ ነገር ብሎኝ . . . . . አዎ ፍለጋውን በተስፋ ማካሄድ እንዳለብን ያለው አልቀረም የናፈቅነውና ፍለጋ የወጣንበት ደግ ዘመን እዚህ ተነኘ

አባ ፡- አዎ ተረባርባችሁ ይዛችሁ ሂዱ . . . .ልጆቼ ዳግም ፍለጋ እንዳትባዝኑ በፍቅር ኑሩ ተዛዘኑ ፣ተረዳዱ ንስሐን ገንዘብ አድርጉ . . . . . .ጊዜ የለንም መሸቶብናልና ።

/ ሁሉም በጎብረት እሺ አባ / ይባረካሉ / ሁሉም በአንድ ላይ ከዚህ በታች ያለውን ግጥም ይናገራሉ ።

ቀዳሚት ተዋህዶ የሐዋርያት
የፍቅር ማህበር ጸጋ በረከት
አትራቂ አትሸሺ አትለይን በእውነት
ከፊት ምሪን እንጂ በመሆን አብነት
ሁሉ እንዲወጣ በአንቺ ቸርነት
ጥዋና መሶቡን ዓለም ሲጥለው
በእኛ ዘንድ ተገኘ የጥንተ አሻራው
ሸክላ ስላሉብህ እንዳይቀየር አደራ
እንደ ገደማይቱ ኑር እንጂ በጋራ
ብርሃን ነውና የጧቱ ጮራ
ዘመነ ሐዋርያት /3/ ትጠራለች .

ሠለስቱ ምዕት ንሕግዘኦ ለሐዋርያ

ፀሐፊ መስከረም ገረመው

1991 ዓ.ም .

‹‹በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐድ አምላክ አሜን››

ዮገና ቁዚጣ

እመቤት ፡- /መጋረጃውን እየከፈተች ቤት ታዐዳለች / ይህ መስታወት እንዴት ቆሸሸ

ናሆም ፡ - ተመስገን አምላኬ በሰላም አሳድረህ ለዚህ ስላደረስከኝ ዛሬ

ልደትህ ነው ምን አባቴ ይዞ ልሂድ / ሀምሳ ብሩን ያወጣል ጠረጴዛ ላይ

ያስቀምጣል / አምላኬ ልቤ ላይ አንተ ንገስ ዛሬ ቀኑ እንዴት ደስ ይላል

ክንዱ ፡- ኤጭ . . . . . ነጋ ደግሞ ዛሬ ምን አይነት ቀን ሆነ በእናታችሁ ፖሪትያችን ሲበላሽ ነው ። ብር

ደግሞ አምስት ሳንቲም የለኝም

አመቤት ፡- እንደ ምን አደራችሁ

ናሆም ፡- እግዚአብሔር ይመስገን

እመቤት ፡- እንኳን አደረሰህ

ክንዱ ፡- እ . . . . /ከጠረጴዛው ላይ ብሩን ያነሳል ቦታው ላይ ይቀመጣል

ናሆም ፡- /ታጥቦ ይመጣል / እመቤት ሀምሳ ብር አንስተሻል

እመቤት ፡- እኔ አልወሰድኩም / ከክንዱ ጋር ይተያያሉ

ናሆም ፡- ክንዱ ሀምሳ ብር አንስተሀል

ክንዱ ፡- ያንተን ሀምሳ ብር ማን ይወስዳል

ናሆም ፡- ሌላ ማን

ክንዱ ፡- ሌባ ማን ነው ሌባ

ናሆም ፡- ሌባ እኮ አላልኩም

እናት ፡- ምንድ ነው ምን ሆናችኃል

ክንዱ ፡- ብሩን የትም ጥሎ ወስደሀል እኮ ነው የሚለው

እመቤት ፡- አይተሀል ነው ያለህ

ክንዱ ፡- ዝም በይ አንቺ ምን አገባሽ

እናት ፡- ፮ረ ክንዱ □ረ አባክ ታናሽ እኮ ነው

ክንዱ ፡- ፮ረ እማሚ እኔም እኮ ታላቅ ነኝ የሚያድግ ልጅ ደግሞ ታላቁ ሌባ ብሎ ያድጋል

እናት ፡-ናሆም የት አስቀም□ው ነው

ናሆም ፡- እ

ክንዱ ፡- ይ□ው እማ ልቡ እኮ ጠፍቷል የሰንበት ተማሪ ነገር አይታመንም አንድ ላይ ጆሬ ጥሎ

ይሆናል

እናት ፡- የምን ጆፌ ምንድ ነው

ክንዱ ፡- ሰው ያልገባውን ሲጠይቀን በጣም ደስ ይለኛል
የአገር ውስጥ ጆፌ ነው ጆፌ ማለት . . . . . .

እናት ፡- ዝም በል እስቲ ስንት ነው የጠፋብህ

እመቤት ፡- ሃምሳ ብር

ክንዱ ፡- እንዴ ደህና የረሳውን ነገር ለምን ተቆሰቁሰብታላችሁ

እናት ፡- በቃ እሰጠሀለው እሺ

ናሆም ፡- አይ እማማ ዛሬ ገና ስለሆነ መባ ልወስድበት ነበር ያሰብኩት ስጦታዬ እግዚአብሔር
አልወደደም ማለት ነው የጠየኩትም አሁን እዚህ አስቀምጠው ሲጠፋ ነው

እናት ፡- ያሰብከውን ስጦታማ ይዘህ ትሄዳለህ እኔ ብር እሰጥሐለሁ

ናሆም ፡- አይ እማ አለኝ

ክንዱ ፡- እኔ አምስት ሳንቲም ኪሴ ውስጥ የለም

እናት ፡- ትናንት የሰጠሁስ ብር

ክንዱ ፡- እኔ እኮ እዚህ ቤት ምን አይነት ጭልፊት እንደገባ አላውቅም ትናንት የሰጠሽው ብር . . .

እመቤት ፡- ሙራድ ጋር ሄደ እዳውን ቀንስለት

ክንዱ ፡- ስለ እገዛሽ አመሰግናለሁ የኛ ሰራተኛ

እናት ፡- □ . . . . □ታ አንተ ልጅ □ ሰው ሁን ልጄ ተው

ክንዱ ፡- እሺ እማ አሁን ስጪኝ እና ልሂድ

እናት ፡- የት ለመሄድ ነው

ክንዱ ፡- ዛሬ እማ በአሉን አስመልክተን ከአዲስ አበባ አንድ ስንዝር መጣ ብለን እንዝናናለን
ይ□ውልሽ እማ ይህ ትኬት ሁለት መቶ ብር የወጣበት ነው

ናሆም ፡- ቀኑ ምን እንደ ታውቂለህ በዚህ ቀን በፍፁም ልብ ጌታ ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅር እና
ለቃሉ ምን ያ□ል ታማኝ እንደሆነ የምታስብበት ቀን እንጂ እንደዚህ በጭፈራና
በሀጥያት የምታሳልፈው ጊዜ አይደለም

ክንዱ ፡- ለእኔ የላብ አደሮች ቀንና ገና አንድ ናቸው

ናሆም ፡- አዎ ምን ልዩነቱን ታውቃለህ በሁለቱም ቀን ትጨፍራለህ ሀጥያትን ትሰራለህ □ረ
ወንድሜ እባክህ ንቃ

እናት ፡- ሰው እስቲ ዩኒቨርስቲን የሚያክል ትቶ እንደዚህ ይገላወጃል

እመቤት ፡- አግብተህ ነበር እንዴ

ክንድ፡- /ይስቃል / አዎ ዩኒቨርስቲ አግብቼ ነበር በሰአት አልተስማንም ፈትቼአት ወጣው

እመቤት ፡- ትዳር ስምምነት ከሌለው አስቸጋሪ ነው ግን

ናሆም ፡- ዝም በይው . . . . እመቤት ዩኒቨርስቲ ማለት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ነው

እመቤት ፡- እሺ

ክንዱ ፡- አሁን አንቺ ኖርሽ ይባላል ዩንቨርስቲን እንኳን የማታውቂ አሁን እኮ እንዲህ ሆነሽ ከሰው እኩል ተሞቻልሽ

እመቤት ፡- ዩኒቨርስቲን ባላውቀው አይጎዳግኝም በጣም የሚጎዳው ግን የላባ አደሮች ቀንና የገና ቀን ልዩነት አለማወቅ ነው ። ይሄንን ሳታውቅ መኖር አይደለም መሞትም ከባድ ነው

ክንዱ ፡- □

እናት ፡- እውነትዋን ነው የላበደሮች ቀን መች ደም አፍሰን እናቃለን ለገና ነው ደም የምናፈሰው

ናሆም፡- ትገርሚያልሽ የሁለቱን ልዩነት ደም በማፍሰስና ባለ ማፍሰስ ገለፅሽው

እናት ፡- ሌላ ልዩነት አለው እንዴ ነፍሱን ይማረውና አባታችሁ ለበአል ምኩት አርዶ ደሙን በምንኖርበትና በምናሰርየው ቤቶች ላይ ሲረጭ ያን ጊዜ ነው በአል በአል የሚለው

እመቤት ፡- ጣራ ላይ ደም መርጨት ምን ጥቅም አለው

ክንዱ ፡- ምንድን ነው አንቺ

እናት ፡- አለው እንጂ

ናሆም ፡- እማማ በአል በአል የሚለው ቀን ምንም የሌላቸውን ስናስብና ስንለግስ ነው ደም መርጨቱ ምንም ጥቅም እንደ ሌለው በቃላት ብቻ አይደለም በተግባር ያለውን ጉዳት አይተሽዋል ስምተሽዋል ግን እግዚአብሔር በይቅር ባይነቱ አሁንም አልተወንም እማ የገና በአል ከበአላት ለየት የሚያደርገ የጥል ግድግዳ የፈረሰበት መላዕክትና ሰው በአንድነ የዘመሩበት በጨለማ የሚኖር ህዝብ ብርሃን ያየበት ትልቅ በአል ነው እኮ እማማ

እናት፡- እሱም መች ካድኩኝ ልጂ

ናሆም - ዘነጋሽው እንጂ እማማ

ክንዱ፡-□ረ በቃችኑ አትጨቃጨቁ በቃ አሁን ስጭኝና ልሂድ

እናት፡- የት ነው የምትሔደው

ክንዱ ፡- ነገርኩሽ እኮ እማማ ይሄ ፓርቲ የአመቱ ምርጥ ፓርቲ ልናደርገው ነው ምክንያቱም እርስ በእርሳችን ስጦታ የምንሰጣጥበት ምርጥ ፓርቲ

እመቤት ፡- እርስ በእርሳችሁ

ክንዱ ፡- አዎ

ናሆም ፡- ልደት የማን ሆነና ነው እርስ በእርሳችሁ የምትሰጣጡት የልደቱ ባለቤት እየሱስ ክርስቶስ ነው ስጦታ የሚገባው ለእርሱ ነው

እናት ፡- ምን አለ ለእርሱ የምንሰጠው

ናሆም ፡- አለ እንጂ እማ ከምስጋና አንስተን እስከ እራስን እስከ መስጠት

ክንዱ ፡- በል ስጥ እኔ ልሂድ

ናሆም ፡- ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ይገቦው የምሄደው የለኝም

ክንዱ ፡- እና

ናሆም ፡- እናማ ዛሬማ ይገቦው የምሄደው አንተን ነው

እመቤት ፡- ለዘመናት ስመኘው የነበረ ነገር

ክንዱ ፡- ለማን

ናሆም ፡- በደሙ ለገዛን እስከ ሞት ድረስ ለወደደን ለእርሱ ለእየሱስ ክርስቶስ

እመቤርት ፡- በእውነት ናሆሜ ጥሩ ስጦታ በስጦታዎች ሁሉ የላቀ ሀምሳ ብር የማይገዛ ስጦታ

ክንዱ ፡- አመሰግናለሁ . . . . እኔ እንደዚህ አይነት ቀልድ አይመቸኝም

እናት ፡- ይዘሀው ልትሄድ

ክንዱ ፡- በሉ ይ□ው ሀምሳ ብርህ እንካ (ቲኬቱን ያስቀምጣል ናሆም ቲኬቱን ያነሳል

ናሆም ፡- ይሄ ነው የሁለት መቶ ብር (200) ሐጥያት መስሪያ

ክንዱ ፡- እንካ ይሄን እርሱን አምጣው

ናሆም ፡- ስንት አመት ሙሉ ቤተ ክርስቲያን ስመላለስ አንተን ወንድሜን ወደ ህይወት መንገድ ማምጣት ሀሳቤዬ ቢሆንም ደፍሬ ግን ለማድረግ አልሞከርኩም ዛሬ ግን ወደ ዚህ ሀጢያት ባህር እንድትሄድብኝ አልሻም

ክንዱ ፡- ምን ለማለት ነው

እናት፡- የሚለውማ ዛሬ የምትሄድበት ቦታ ዳግም ላትመለስበት ትተህ ዛሬ በልደቱ የክርስቶስ ስጦታ ሁንልኝ ነው የሚልህ . . .. እንዛ ዓይደል እመቤት

እመቤት ፡- አዎ እችን የልደት ቀን ስንት ነብያት ለማየት ወደው ነበር ግን አላይዋትም ስለዚህ በህይወት ሳለህ እቺን ቀን ሳታያት እንዳታልፍ ዛሬ ነውና ቀንህ እያት ነው የሚልህ . . . . . እንግዛ ነው አይደል ናሆሜ

ክንዱ ፡-እሺ ሌላ ግዜ እሄዳለሁኝ አሁን ትኬቱን ስጠኝ

ናሆም ፡- ትኬቱን /ይቀዳድዋል / ለእናቱ ይሰጣታል እናም ትቀደዋለች

ክንዱ ፡- ቀደድከው እንዴ ሁለት መቶ ብር (200) እኮ ነው የወጣበት ያለ ትኬቱ ደግሞ መግባት አልችልም

እናት ፡- እሰይ . . .. . እልል እልል

ክንዱ ፡- እንዴ እልል ትያልሽ

እናት ፡- ምን ላድርግ ደስታ እኮው ነው ያለ ትኬቱ አለመግባትህ ደስ ብሎኝ እኮ ነው አንተ እኮ ጥሩ ልጅ ነህ በጓደኞችህ አጉል ምክር ተስበህ ነው እንጂ ልጄ እማ ጥሩ ነህ

እመቤት ፡- አዎ ክፉ ባለ እንጀራ መልካሙን አመል ያጠፈዋል አይደል የሚለው ቃሉ

ክንዱ ፡- እኔ የምሰራውን አውቃለው

ናሆም ፡- ብታውቅ የእግዚአብሔርን ጥሪና የሰይጣንን ጥሪ ትለይ ነበር

ክንዱ ፡- አንተ ልጅ ተወኝ ስሜን እዳትጠራ ካሁን ቡኃላ

ናሆም ፡- እንዴት ልተውህ ክንድ አንተ ወንድሜ ወደ እሳት ውስጥ ስትገባ እንዴት ዝም ልበል ዛሬ እንኳን የአምላክን ጥሪ ቸል አትበል

እመቤት ፡- መቼም እግዚአብሔር ሰውን የሚጠራበት የተለያዩ ምክንያት አለው እስቲ ዛሬ ዝም ብለህ ሂድ

ክንዱ ፡- ከዛስ

እናት ፡- ከዛ እማ እግዚአብሔር በቤቱ ያፀናሀል እንደ ወንድምህ ታገለግላለህ በል አሁን ማመንታት አያስፈልግም እንሂድ

ክንዱ ፡- ሀሳባችሁን ብቀበለውም ዛሬ ግን . . .. እኔ አልሄድም

እመቤት ፡- ለምን

ክንዱ ፡-እመቤት ብዙ ኃጥያት አለብኝ ከነ ኃጥያቴ አልሄድም ባይሆን ሌላ ጊዜ ፀበል ተጠመቂ እሄዳለው

ናሆም ፡- ክንዱ ዛሬናት ያንተ ቀን አምላካችን ያለው እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ወደ ኑ ነው እንጂ ያለው እናንተ ንጹሀን ወደ ኔ ኑ አላለም ስለዚህ ከነ ሸክማችን ሄደን ሸክማችንን ጥለን እንመለሳለን

ክንዱ ፡- እና ልሂድ

ናሆም ፡- አዎ ወንድሜ

ክንዱ ፡- ይቅርታ

ናሆም ፡- ና እቀፈኝ (ይተቃቀፋሉ) (እናት እልል) ክንዱ እንካ ሀምሳ (50)ብርህን

እመቤት ፡- ወይኔ ደስ ሲል

እመቤት ፡- የላበደሮችና የገና በአል ልዩነት ዛሬ ታወቀ የገና በአል ደስ ሲል

ናሆም፡- በሉ ሁላችንም ለልደቱ ባለቤት ስጦታችንን ይዘን ወደ ማደሪያው እንሂድ

እመቤት ፡- በቃ እኔም ቡኃላ አፀደዋለሁ /መጋጃው ይዘጋል /

ድርሰት

ቢንያም ታደሠ

እና

የኃላሸት ወ/ሚካኤል

ቀን ታሕሳስ 11/4/2002 ዓ.ም

ሠላም ለኽሊዘ-በሐር

‹‹በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐድ አምላክ አሜን››

ምግባር

/መጋረጃ ሲከፈት አቶ አየለ ቁጭ ብለው ሬዲዮ እያደመጡ ሰው ይመጣል /

አየለ ፡- ወዴት ነው ወዴት ወዴት

ሰው ፡- ፮ረ ጋሽ አዬ ቸኩዬ ነው

አየለ ፤- ቢሆንስ አንተ ይህ የአባት ቤት ነው እንዴ ዝም ብለህ ዘው የምትለው

ሰው ፤- እንዴ ጋሼ አላወቁኝም

አየለ ፤- ባቅህስ በል አሁን እጅህን ዘርጋ /ይተሻሹታል / በል ግባ ከውካዋ

ሰው ፡- /እሺ ይገባል/

አየለ ፤- ምን እንዳው ሰው እኮ ጤና አጥቷል ምን አይነት ከውካዋ ነው / ግሩም ይገባል /

ግሩም ፡- ደህና ዋሉ አቶ አየለ

አየለ ፡- እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ እርሶ እንዴት ኖት

ግሩም ፡- ክብር ይግባው ለፈጣሪ ደህና ነኝ ኑሮ እንዴት ነው አቶ አየለ

አየለ ፡- ጥሩ ነው እግዚአብሔር ይመስገን

ግሩም ፡- እሺ በሉ /ይሄዳሉ/ ይፈትሹኝና ልግባ

አየለ ፤- እንዴ እርሶን በፍፁም ጌታዬ የማይሆነውን

ግም ፤- እሺ /ይገባል /

አየለ ፡- አይ ሰው አይ ደግነት ምንም እንኳን የማይወጣላቸው ጥሩ መልካም ሰው እውነትም የእግዚአብሔር ሰው ፈጣሪ የሚፈሩ ሰው የሚያከብሩ

አስናቀች ፡- አየለ ምን ሆነህ ነው ብቻህን የምታወራው /ነጠላ እየቋጨ ትገባለች /

አየለ ፡- የእኚህ ሰው ትህትና እየገረመኝ ነዋ አስኒዬ

አስናቀች ፡- የትኛው ሰው

አየለ ፡- የአቶ ግሩም ነዋ

አስናቀች ፡- የእሳቸው ምግባር እንዲያው በቃል ብቻ ተነግሮ የሚያልቅ ነው ስራቸውን አክባሪ ትሁት

አየለ ፡- ስልጣን እያላቸው አይኮሩ ጥሩ ደሞዝ እያላቸው ከሚስኪኑ ጋር ሚስኪን ድሀ ሀፍታም ሳይሉ ሁሉም በእኩል በማየት የተበላሸውን መክረው አረ ስንት ነገር አድርገዋል

አስናቀች ፡- እሳቸውን የወለዱ ቤተሰባቸው እንዴት ታድለዋል የሰው መላክ እኮ ናቸው ፡፡

አየለ፡- ልክ ነሽ እሳቸው የሰው መላክ የሰው መላክ እኮ ናቸው /ታደሰ ይገባል /

ታደሰ ፡- ጋሽ አየለ በአስቸኳይ ይጠራሉ ኑ

አስናቀች ፡- ሁለታችን ነው

ታደሰ ፡- አዎ በአስቸኳይ ኑ

አየለ ፡- ምናው ታደሰ የተፈጠረ ነገር አለ እንዴ

ታደሰ ፡- መሰለኝ በሩን ቆልፋት ማንም ሰው መግባትም ሆነ መውጣት አይችልም ተብሏል ፡፡

አስናቀች ፡- ምን ተፈጠረ ደግሞ

ታደሰ ፡- እኔ ምን አውቃለሁኝ ስራ አስኪያጃችን ሁሉንም ሰብስበልኝ ብለዋል

ስራ አስኪያጅ ፡- እንደ ምን ዋላችሁ በጣም የሚገርም ነገር ልነግራችሁ ነው ባለፈው የጠፋው እቃ ተገኘ

መሰሉ ፡- ምን ?የት?

ስራ አስኪያጅ ፡- እርሷ እኛን ገርሞናል ለማንኛም በሩን ዝጉ ማንም እንዳይወጣ አቶ ግሩም ጋር እንሂድ እርሳቸው ቢሮ የምናወራው ጉዳይ አለ ፡፡ (ሁሉም ያወጣሉ)

ገቢር ሀለት(2)

/ አቶ ግሩም ወንበር ላይ ተቀምጠው እየሰሩ ሰራተኞች ይገባሉ ከስራ አስኪያጁ ጋር /

ስራ አስኪያጅ ፡- ደህና አደሩ አቶ ግሩም

ግሩም ፡- እግዚአብሔር ይመስገን አለቃዬ የተፈጠረ ነገር አለ ሰራተኛው ምን ሆነ

ከበደ፡- አቶ ግሩም ሰራተኛ ይገፍ የመጣሁት አጭር ስብሰባ እንድናደርግ ነው

ግም ፡- ታድያ ይቀመጡ

ከበደ ፡- ቆሜ እናገራለሁኝ እርሶ እንደ ሚያውቁት በዚህ መስሪያ ቤት በየጊዜው ትላለቅና ትናንሽ እቃዎች ይጠፋሉ ነገር ግን የሚሰረቀው ከዚህ መስሪያ ቤት መሆኑ ሆላችን ጥርጣሬ ቢኖረንም ማናችንም አላወቅንም ይባስ ብሎ ዛሬ በጠዋት የሂሳብ ክፍል ኤሌክትክ አዲንግ ማሽን ጠፋ

ግሩም ፡- ዛሬም ጠፋ

ከበደ ፡- አዎን ዛሬ ግን እንደ በፊቱ ጠፋ ብለን የምንተወው አይደለም ሁሉም ሰራተኛ ከግቢ መውጣት አይችልም የሁሉም ቢሮ ይፈተሸል ስለዚህ እርሶ እንዲሳተፉ ነው

ግም ፡- ይቅርታ አድርጉልኝና ትንሽ የጀመርኩት ስራ አለ እኔ ብቀር ደስ ይለኛል

ከበደ ፡- ጥሩ እኔ ስራ አለኝ ካሉ ሁላችም በየ ቢሮ ፍተሸ እናደርጋለን ፍተሻው በሁለት ጥበቃ ሰራተኛ በኩል ይከናወናል

አየለ ፡- ጌታዬ ይህ የጠፋው እቃ የተገኘበት ሰው ሁላችንም ስራ አስፈትቶ ስላስዋለን ከፍተኛ ቅጣት መቀጣት አለበት ፡፡(ሁሉም አዎን መቀጣት አለበተ)

ሁሉም ከወጡ ቡኃላ

ግሩም ፡- በዚህ መስሪያ ቤት ያለው ጥፋተኛ ማነው

ዘነበ ፡- (በፍርሀት) አቶ ግሩም . . . . . አቶ ግሩም . . . . . .

ግም ፡- አቤት ዘነበ ምን ሆንክ

ዘነበ ፡- እባኮትን የዛሬውን ይቅር በሉኝ መዋረዴ ነው

ግሩም ፡- ምን ችግር ገጠመህ

ዘነበ ፡- የለመደ እጄ ዛሬ ጉድ አደረገኝ ሰይጣን አሳሰተኝ

ግም ፡- የሆንከውን ንገረኝ

ዘነበ ፡- የበፊቱ አልበቃ ብሎኝ ሰራተኛው እቃ ሲጠፋበት በሀላፊነት ተቀብልአልና ይከፍላል ዛሬ የጠፋውን እቃ እኔ ነኝ የወሰድኩት ሌላ ሰው ላስከፍል

ግም ፡- ዘነበ ምን ነካህና ሌብነት ገበ ህ ደሞዝ አነሰህ

ዘነበ ፡- ልማድ ቅብጠት አመል ሆነብኝ ነው እባክት የሆነ ዘዴ ይንገሩኝና ከውርደቱ ደብቁኝ

ግሩም ፡- በል አምጣው መሳቢያ አስገባው በዚህ ማስቀመጥህን ለማንም አትናገር

ዘነበ ፡- በመደነቅ እውነቶትነው እኔ እኳ ስንት ትልቅ ነገር ሲጠፋ ሰራተኛ ከመክፈል ውጭ ፈተሻ አልተደረገም

ግሩም ፡- አዎን ለወደፊቱ አይለምድህም ፈጣሪን ለምን በንስሀ ተመለሰ ከሰው የደበከው ከአምላክ አይደበቅምና

ዘነበ ፡- ፈጣሪ የዛሬን ያውጣኝ እንጂ ነገን ምን መሆን እንዳለብኝ እኔ አውቃለሁ

ግሩም ፡- በል ሂድ ከሰው መካከል ከጠፋ ሌላ እንዳያህ ሂድ የመዳን ቀን ዛሬ ነው

ዘነበ ፡- ፈጣሪ ያክብሮት ደህና ዋሉ

ግሩም ፡- አቤቱ ፈጣሪ አንተ አፅናኝ አበርታኝ

ገቢር ሶስት (3)

/ከውጭ ይገባሉ ሁሉም ግሩም ቢሮ/

ከበደ ፡- አቶ ግም ይቅርታ አድርጉልኝ አንተን እንኳን በእውነት መጠርጠር የለብኝም ግን ሁሉም ቢሮ ክፍሎችን ፈልገን አጣን የቀረን ይህ ቢሮ ነው ፍቃደኛ ብትሆን ለደንቡ ያህል ብትፈትሽ

ግሩም ፡- ማንን ማን ያውቃል ፈልጉ እኔ ከሌላው ሰራተኛ በምን እለያለሁኝ ይፈተሽ ምኔ ታምኖ ሳልፈተሽ ልቅር /መፈተሽ ይጀመራል/

አየለ ፡- አረ ምን ጌታዬ የጠፋው እቃ ይኸው ተገኘ ጉድ ጉድ

ከበደ ፡- / በመደንገጥ / አቶ ግሩም ይህን እቃ አንተ ነው የወሰድከው ለስራ ፈልገ□ው ነው ወይስ

ታደሰ፡- ጌታዬ ምን ጥያቄ ያስፈልገዋል ከቢሮአቸው ተገኝቶ ሰርቆት ነው እንጂ ወራዳ

አየለ፡- ይገርማል እስከ ዛሬ ሰውአርገን ስንቆጥራቸው ለካስ ምላጭ ነበሩ እኔ እንኳ በር ላይ እንኳን አልፈትሻቸውም ነበር

ከበደ፡- አዝናለው አቶ ግሩም በዚህ አይነት አልጠረጥርህም ነበር ሌባ ነህ ለካስ አስከ ዛሬ አንገትህን ደፍተህ ጉድ ስታደርገን የነበረው አንተ ነበርክ ለካስ የጭቃ ላይ እሾህ ነህ

አስናቀች ፡- እኔም ድሮም ይቀፈኝ ነበር ሰው መሳይ በሸንጎ ቀጠፍ አንገቱን ደፍቶ ሊዘርፈን ነበር ።

አየለ፡- ቅድም አልነገርኩሽም የሰው ሰይጣን ብዬ እኔ እኳ የምናገረው ከመሬት ጠብ አትልም

ታደሰ፡- እንደዚህ አይነት የጭቃው ላይ እሾህ የሆነ ሰው ይዘን መሔድ አንችልም

ከበደ፡- ሠራተኞች ሀሳብ ለመስጠታቸው በፊት ጥያቄ ልጠይቅህ እስከ ዛሬም የነበረውን የጠፋ እቃ የወሰደከው ሰው አንተ ነህ ትሰማኛለህ ግሩም መልስልኝ

አየለ፡- ስንት እቃ ወሰድክ ምን ግሩም እርጉም ነው

መሰለ፡- ምን ምን ወስደክ ይሆን እርጉም

አስናቀች ፡- አይናገርም እንዴ ንቀት ነው መልስ መስጠት ካልቻልክ ሁላችሁም ፍርድስ ስጡት /በጥፊ ይመቱታል/

ታደሰ፡- ምን ፍርድ መስጠት ነው ማሸት ነው እንጂ (ይመቱትና ይወድቃል)

ከበደ፡- በቃችሁ ፖሊስ ጣቢያ ደውለን ለህግ መስጠት እንጂ መምታት ለምን

መሰለ ፡- ግታዬ እንደ እኔ እንደ እኔ ይሔን ሁሉ ሰራተኛ ጥሩ ሰው መስሎ ማታለል ይቅርታ የሚገባው አይደለም በሞት ደስ ይለኛል

አየለ ፡- ለምን ፖሊስ ለምን መጥቶ አይወስደውም

አስናቀች ፡-የምን ፖሊስ እዚህ ቀጥቅጠን እንግደለው ሌባን መግደል መንግስት ይደግፈናል

ግሩም ፡- ደበደባችሁኝ ሰደባችሁኝ ሰው ሆኖ የማያጠፋ የለም አጥፋቸው ግን ክፋቱ የከፋ ቢሆንም ከስራ . . . አታባሩኝ እቃው ቢያንጓጓኝ ሰረኩት ደስ ቢሰኝ ወሰድኩት እና ይበቃኛል መደብደቤ

አየለ ፡- ደግሞ አፍ አለኝ ብሎ ያወራል ከመስሪያ ቤት አይደለም አንተንማ ከሀገር ነው ማበረር በዚህ ሌላ አለም ቢኖርም ከዚህ አለም ነበር ማባረር ከንቱ የከንቱ ከንቱ ምት

አስናቀች ፡- እኔ እኮ የሚገርመኝ እንደ ርግብ የዋህ መስሎ እንደ እባብ ነደፋኝ አንተን ብሎ ክርስቲያን

መሰሉ ፡- የእግዚአብሔር ሰው መስሎ ለካስ የቀበሮ ባህታዊ ኖራሃላ

ከበደ ፡- እናም ምን ትላላችሁ ከስራ ይባረር አይባረር

ታደሰ፡- ከስራማ እማ መባረር አለበት ሌባ እማ መስሪያ ቤታችን መኖር የለበትም አሁኑኑ ከፊትችን ይሂድ

ዘነበ ፡- በቃችሁ ጌታዬ ይቅርታ አድርጉልኝ እስካሁን ዝም ብዬ ነበር አቶ ግሩም አሁንም ጥሩ መልካም ሰው ናቸው ደግ ሰውም ናቸው ሌባም ቀጣፊም አይደለም ለኛ ሊያስተምር ሌባ ሳይሆን ሌባ ተባሉ

አየለ ፡- አይ ይሄ አብረህ ሰርቀህ እንዳይሆን እንጂ

አስናቀች ፡- ወረኛ ነህ

ዘነበ ፡- ሌባ እሳቸው ሳይሆኑ . . . . .እኔ . . .. . ነኝ

ከበደ፡- ምን ምንድን ነው የምታወራው

ግሩም ፡- ዘነበ ተው ሲያከብሩኝ ነበረ እንዲያውም ሰውነቴን ትተው መላክ ስሉኝ አሁን ግን ሰይጣን አሉኝ ተዋቸው እኔ በትምክት እንዳልወድቅ ይጠምቀኛል ውርደቴ

አየለ ፡- ድሮም ያሳትከን አንተ ነህ

ዘነበ፡- አቶ ግሩም ደግ ናቸው ለእኔ መስዋእት ሆኑ ያለ ጥፋታቸው ተደበደቡ ተወቀሱ ተሰደቡ አልነኩም አመል አለቅም ቢለኝ የሰረኩት እኔ ነኝ

ታደለ ፡- እኔ ነኝ

መለሱ ፡- አማረልኝ ብለህ አታውራ

ዘነበ ፡- በዚህ ቤት ሁሉ የጠፋውን እቃ ሁሉ የሰረኩት እኔ ነኝ

ከበደ፡- ታዲያ እቃው የተገኘ የት ነው አነት ቢሮ ሳይሆን በእሳቸው ቢሮ አይደለ ምን ማን አመጣው

ዘነበ ፡- አድምጡኝ እንደ ለመድኩት ዛሬም ይህን እቃ አነሳው በመጨረሻ ወደ ፍተሻ ሲገባ ወደ አቶ ግሩም መጣው አማከርኳቸው እኔ ከምዋረድ ብለው ተዋረድሉኝ የሰረኩት እኔ ነኝ

ከበደ ፡- አቶ ዘነበ የምታወራው እውነት ነው

ዘነበ ፡- አዎ አዎ እውነቴን ነው እኔን አባርሩኝ እኔን ግደሉኝ እኔን እሰሩኝ እሳቸው ንፅሁ ናቸው

ከበደ ፡- በሉ ለካስ ሌባው አንተ ነህ ግሩምን ልቀቁት ዘነበ ፖሊስ ጥሩና ይዘውት ይሂድ አቶ ግሩም ይቅርታ አድርግልን ጥሩ ምግባር አሳየኸን ይህ ነው ያሳተን

አየለ፡- ኧ እንዴት ያለ ትእግስት ነው ያቀረበልን

አስናቀች ፡- ምን አፍ አለኝ እባኮት ይቅርታ አድርጉልን

ታደሰ ፡- ይህ ክፉ በስራ አሳሰተን

መለሱ ፡- ክብሩን ሰው ክፉ አደረግን

ከበደ፡- እንዳትመቱት ፖሊስ ጥሩ

ግሩም ፡- እኔ ይቅር እንድላችሁ ይቅር በሉት ዘነበ በእኔ የወረደውን ድላ ፈርቶ ነበር ወደ እኔ ያመጣው እኔም ዱላውን ተቀብዬለታለሁ ይቅር በሉት

ከበደ ፡- ሌባን አቶ ግሩም በመምታታችን አዝናለሁ ዘነበ ግን ይቅርታ አይባልም

አየለ ፡- ክብሩን ያዋረደ ዘረፋ ተሳስቶ ከስህተት ጨመረን

አስናቀች ፡- እኛ ያሳሰተ ደፋር

ግም ፡- ይቅር በሉት ተሳስቶ ነው ልክ እናንተ በእኔ ላይ የተሳሳታችሁትን መሳታት ሁላችሁም ምንም ሰው ቢያጠፋ ከቻላችሁ ንገሩት ነገር ግን አትደብድቡት ዘነበ ቢሰርቅ እኛ ስንት ሀጢያት ሰራን የአማን ፣የዋሸን ፣ ሁላችን አንድ ነን የሀጢያት ትልቅ ትንሽ የለውምና

ከበደ ፡- በሉ ልቀቁት እርሱም ይቅር ብሎናል

ዘነበ ፡- አቶ ግሩም ይቅርታ አይገባኝም ልሙት ልወገር ኃጢያተኛ ክፉ ነኝ ራስ ወዳድ

ግሩም ፡- ሁላችን ይቅር እንባባል ያለፉን ትተን በአዲስ እንኑር ፈጣሪ ይቅር እንዲለን ይቅር እንባባል አትበሉ ብሎን በላን በልተን ትእዛዝ እንሸር ወድቀን ሲፈልገን ምን ደግ ስራ አልነበረንም ወደድን ጥሩ ሳንሆን አፋቀረንም መልካም አከበረን እሾህ አክሊል አድርገው ሲተፉት በመስቀል ሲሰቀል ምህረትን ይለምን ነበር ሁላችንም ምግባር ይኑረን

አየለ ፡- አይ ልጄ አንተን ምን ሲባል ይቅርታን ትእግስትን ምግባርን መስዋእትነትን አስተማርከን ዘነበንም ይቅር ብለናል ለወንድምህም አሳልፈህ ሰጠህ

ግሩም ፡- ዘነበም ንቃ ሁላችንም እንቃ የመዳን ቀን ዛሬ ነው ከመንበት ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቧል እነሆ በደጁ ቆሜ አንኳኳለሁ በሩን ቢከፍትልኝ ወደ እርሱም እገባለው ከእርሱም ጋር እራት እባላለው ብሉአል እናንተ ሸክማችሁ የከበደውን እኔ ኑ ሸክማችሁን አረግፍላችኃለሁ ሻክሜ ቀሊል ቀንበሬም ልዝብ ነውና እሺ በትሉ ብትታዙ የምድርን በረከት እንቢ ብትሉ ግን ሰይፉ ይበላችኃል

ሁሉም ፡- ይቅር ብለናል

ግሩም ፡- እግዚብሔር ይቅር ይበላችሁ

